## ከእስልምና ህግ ታላቅነት ገጽታዎች አንዱ መቻቻልና ገርነት ነው

ምስጋና ሁሉ በተከበረው መጽሐፉ

{ يُرِيدُ اللَّهُ بِكُمُ الْيُسْرَ وَلَا يُرِيدُ بِكُمُ الْعُسْرَ }

ለአለው ለአለማቱ ጌታ ለአላህ ይገበው፡፡ ትርጉሙም (አላህ በናንተ ገሩን (ነገር) ይሻል፡፡ በናንተም ችግሩን አይሻም፡፡) ማለት ነው፡፡

ብቸኛ ከሆነው ለሱም አጂጋሪ ከለለው አላህ በስተቀር በእውነት የሚገዙት አምላክ እንደሌለ እመሰክራለሁ፡፡ እንዲሁም በተከበረው ሓዲሳቸው (እኔ የተላኩሁት ገራገር በሆነው ቀጥተኛ መንገድ ነው፡፡) ያሉት ነብያችን ሰይዲና ሙሐመድም የሱ ባሪያና መልእክተኛ በመሆናቸውም እመሰክራለሁ፡፡ ጌታዬ ሆይ! በርሳቸው፣ በቤተሰቦቻቸው፣ በባልደረቦቻቸውና እስከ እለተ ቂያማ ድረስ በመልካም ምግባር በተከተሏቸው ምእምናን እዝነትህን፣ ሰላምህንና በረከትህን አውርድ፡፡

**ከዚህም በመቀጠል፡፡**

የእስልምና ህግጋት ታላቅነት ገጽታዎች ቁጥር ስፍ የሌላቸው መሆኑ ጥርጥር የለበትም፡፡ የእስምና እምነት ከተለየበት ታላቅና ብሩህ ገጽታም ቃላቱ ባዘሉት ታላቅ ፍች የመቻቻልና ገርነት ገጽታው ነው፡፡ በእምነቱ ችግርም ሆነ አስጨናቂ ነገር እንዲሁም የማጥበቅም ሆነ የማከረር ገጽታ አይታይበትም፡፡ እዚህ ላይ በእምነቱ ተከታይነት የሚካተቱና በሃይማኖት ጥንቁቅ ለመሆን ማጥበቅን ግድ እንደሚል የሚገምቱ አንዳንድ አጥባቂዎች ማከረር የእምነቱ ጉድለት ሊሆን እንደማይገባ መገንዘብ ያስፈልጋል፡፡
የነዚህ ወገኖች አመለካከት ደንብን መጠበቅና ጥንቁቀነት በሚል ስያሜ በጸንፈኝነት ጎዳና በዙዎችን እያግበሰበ የሚወስድ በር በህዝቡ ዘንድ በሰፊው የከፈተ ከመሆኑም ባሻገር ጸንፈኝነት በጣም ያጠበቀ እውነተኛ ምእምንና ፈሪሀ አላህ ነው በማለት በዙዎቹ የሚፎካከሩበት ሰፊ መደረረክ ሆኗል፡፡
ይህ ተግባራቸው ታድያ የሚያመለክተው ነገር ቢኖር ስለእምነቱ ታላቅነት፣ ስለአዘለው የመቻቻልና የገራገርነት ገጽታ ጥልቅ ግንዛቤ የሌላቸው መሆኑን ነው፡፡ አላህ (ሱ.ወ.) እንድህ ይላል፡

وَمَا جَعَلَ عَلَيْكُمْ فِي الدِّينِ مِنْ حَرَجٍ ۚ مِّلَّةَ أَبِيكُمْ إِبْرَاهِيمَ ۚ هُوَ سَمَّاكُمُ الْمُسْلِمِينَ مِن قَبْلُ وَفِي هَٰذَا لِيَكُونَ الرَّسُولُ شَهِيدًا عَلَيْكُمْ وَتَكُونُوا شُهَدَاءَ عَلَى النَّاسِ}

ትርጉሙም (በናንተም በሃይማኖቱ ውስጥ ምንም ችግር አላደረገባችሁም፡፡ የአባታችሁን የኢብራሂምን ሃይማኖት ተከተሉ፡፡ እርሱ ከዚህ በፊት ሙስሊሞች ብሎ ሰይሟችኋል፡፡ በዚህም (ቁርአን) መልክተኛው በናንተ ላይ መስካሪ እንዲሆን እናንተም በሰዎች ላይ መስካሪዎች እንድትሆኑ (ሙስሊሞች ብሎ ሰይሟችኋል)፡፡) ማለት ነው፡፡
ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) አንድህ ይላሉ (ሃይመኖት ገር ነው፡፡ አንድም ሰው ሃይማኖትን ትግል አይገጥምም የሚያሸንፈው ቢሆን እንጅ፡፡ ትክክለኛዎች ሁኑ፡፡ (ካልቻላችሁ) ወደትክክለኛነት የተቃረባችሁ ሁኑ፡፡ ማለዳ፣ ወደማታ ላይና በጥቂቱ ሌሊት መልከም ሥራን ሥሩ፡፡ በነዚህ

ጊዚያት ተገቢውን ተግባር ማከናወን ይቀላልና፡፡) ሱፍያን አሰውሪ የተባሉት ሊቅ እንድህ በማለታቸወው እጅጉን ይደነቃሉ፡ ‹ከኛ ዘንድ እውቀት የምንለው በአመኔታ የተሰጠንን ፈቃድ መጠቀማችንን ነው፡፡ ማከረርንማ ማንም ሰው ይችልበታል፡፡›
በእስልምና ህግ መቻቻል በምላስ የምንናገር ቃል ወይም የምናነግበው መፈክር ብቻ ሳይሆን መለኮታዊ የሕይወት ስርኣትና አላህ (ሱ.ወ.) ከባሮቹ ጋር የተዋዋለበትና ከመካከላቸውም በሱ እንዲዋዋሉ ትእዛዝ የሰጠበት መርህ ነው፡፡ አላህ (አ.ወ.) እንዲህ ይላል፡
{لَا يُكَلِّفُ اللَّهُ نَفْسًا إِلَّا وُسْعَهَا}
ትርጕሙም (አላህ ነፍስን ከችሎታዋ በላይ አያስገድዳትም፡፡) ማለት ነው፡፡ እንድሁም በሌላ አንቀጽ እንድህ ይላል፡
{ يُرِيدُ اللَّهُ بِكُمُ الْيُسْرَ وَلَا يُرِيدُ بِكُمُ الْعُسْرَ}
ትርጕሙም ((አላህ በናንተ ገሩን (ነገር) ይሻል፡፡ በናንተም ችግሩን አይሻም፡፡) ማለት ነው፡፡
አሁንም በሌላ አንቀጽ እንድህ ይላል፡
{يُرِيدُ اللَّهُ أَنْ يُخَفِّفَ عَنْكُمْ وَخُلِقَ الْإِنْسَانُ ضَعِيفًا}
ትርጕሙም (አላህ ከናንተ ሊያቀልላችሁ ይሻል፡፡ ሰውም ደካማ ሆኖ ተፈጠረ፡፡) ማለት ነው፡፡
በአላህ መጽሐፍ ለሁሉም ባሮቹ የተስፋን፣ የምህረትንና የአዝነትን በር በመክፈት ሰፊ ተስፋ በሚጣልባት አንቀጽም አላህ (ሱ.ወ.) እንድህ ላል፡
{قُلْ يَا عِبَادِيَ الَّذِينَ أَسْرَفُوا عَلَى أَنْفُسِهِمْ لَا تَقْنَطُوا مِنْ رَحْمَةِ اللَّهِ إِنَّ اللَّهَ يَغْفِرُ الذُّنُوبَ جَمِيعًا إِنَّهُ هُوَ الْغَفُورُ الرَّحِيمُ}
ትርጕሙም (በላቸው እናንተ በነፍሶቻችሁ ላይ ድንበር ያለፋችሁ ባሮቼ ሆይ! ከአላህ እዝነት ተስፋ አትቁረጡ፡፡ አላህ ኃጢአቶችን በመላ ይምራልና፡፡ እንሆ እርሱ መሃሪው አዛኙ ነውና፡፡) ማለት ነው፡፡ እንድህም ይላል፡
{ وَرَبُّكَ الْغَفُورُ ذُو الرَّحْمَةِ}
ትርጕሙም (ጌታህ መሃሪው የእዝነት ባለቤት ነው፡፡) ማለት ነው፡፡ እንድህም ይላል፡
{إِلَّا الَّذِينَ تَابُوا وَأَصْلَحُوا وَبَيَّنُوا فَأُولَئِكَ أَتُوبُ عَلَيْهِمْ وَأَنَا التَّوَّابُ الرَّحِيمُ. {
ትርጕሙም (እነዚያ (ከመደበቅ) የተጸጸቱና (ስራቸውን) ያሳመሩ (የደበቁትን) የገለጹም ብቻ ሲቀሩ፡፡ እነዚያም በነሱ ላይ (ጸጸታቸውን) እቀበላለሁ፡፡ እኔም ጸጸትን በጣም ተቀባይ አዛኙ ነኝ፡፡ ) ማለት ነው፡፡ (ከርሳቸው አላህ ይውደድና) አቡ ሁረይራህ የሚከተለውን አውርተዋል፡ ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) እንድህ አሉ፡ (አላህ (አ.ወ.)ፍጥረታትን በፈጠረበት ጊዜ እሱ ዘንድ ከዙፋኑ በላይ እዝነቴ ቁጣዬን ይቀድማል የሚል ቃል ጻፈ፡፡) አለህ (ሱ.ወ.) በተቀደሰ ሓዲስ እንዲህ ይላል፡ (ያድም ልጅ ሆይ! አንተ በጸለይከኝና ተስፋ በጣልከብኝ ጊዜ አንተ የፈጸምከውን ሁሉ ኃጢአት ከምንም ሳልቆጥር ምህረት አድርግልሃለሁ፡፡ ያድም ልጅ ሆይ! ኃጢአትህ ሰማይ የነካ ከሆነ በኋላ ምህረት ብትጠይቀኝ ብዛቱን ከምንም ሳልቆጥር ምህረት አደርግልሃልሁ፡፡ ያድም ልጅ ሆይ! አንተ በምድር ሙሉ የሚሆን ኃጢአት ተሸክመህ በኔ ማነንም ሳታጋራ በትገናኘኝ በምድር ሙሉ ምህረት አዘጋጅቼ እጠብቅሃለሁ፡፡
አላህ (ሱ.ወ.) በተከበረው መጽሐፉ በበርካታ ቦታዎች ባሮቹ ምህረት እንዲያደርጉና ነገሮችን በትእግስት እንዲያሳልፉ አዟል፡፡ እንዲህም ይላል፡
{ خُذِ الْعَفْوَ وَأْمُرْ بِالْعُرْفِ وَأَعْرِضْ عَنِ الْجَاهِلِينَ}
ትርጕሙም (ገርን ጠባይ ያዝ፡፡ በመልካምም እዘዝ፡፡ ባለጌዎችንም ተዋቸው፡፡) ማለት ነው፡፡
እንድህም እንድህ ይላል፡
{ وَلَا تَسْتَوِي الْحَسَنَةُ وَلَا السَّيِّئَةُ ادْفَعْ بِالَّتِي هِيَ أَحْسَنُ فَإِذَا الَّذِي بَيْنَكَ وَبَيْنَهُ عَدَاوَةٌ كَأَنَّهُ وَلِيٌّ حَمِيمٌ * وَمَا يُلَقَّاهَا إِلَّا الَّذِينَ صَبَرُوا وَمَا يُلَقَّاهَا إِلَّا ذُو حَظٍّ عَظِيمٍ}

ትርጉሙም (መልካሚቱና ክፉይቱም (ጠባይ) አይተካከሉም፡፡ በዚያች እርሷ መልካም በሆነችው ጠባይ (መጥፎይቱን) ገፍተር፡፡ ያነ ጊዜ ያ ባንተና በርሱ መካከል ጠብ ያለው ሰው እርሱ ልክ እንደአዛኝ ዘመድ ይሆናል፡፡) ማለት ነው እንድህም ይላል፡

وَلْيَعْفُوا وَلْيَصْفَحُوا أَلَا تُحِبُّونَ أَنْ يَغْفِرَ اللَّهُ لَكُمْ وَاللَّهُ غَفُورٌ رَحِيمٌ. {

ትርጉሙም (ይቅርታም ያድርጉ (ጥፋተኞችን) ይለፉም፡፡ አላህ ለናንተ ሊምር አትወዱምን? አላህም መሃሪ አዛኝ ነው፡፡) ማለት ነው፡፡

የነብያችንን (ሰ.ኢ.ወ.) የሕይወት ታሪክ የሚከታተል ሰው አሳቸው በመቻቻልና ነገሮችን በማቃለል ልህዝቦቻቸው ብሎም ለሰው ልጅ ሁሉ ምን ያማሩ አርአያ እንደነበሩ በግልጽ ሊገነዘብ የሚችል መሆኑ አያጠራጥርም፡፡ ይህን ጉዳይ ሲገልጹ እናታችን አዒሻ እንድህ ብለዋል፡ (የአላህ መልክተኛ ከሁለት ነገሮች መካከል እንዲመርጡ ተጠይቀው አያቁም ወንጅል የሌለበት እስከ ሆነ ድረስ ቀለል ያለውን የመረጡ ቢሆን እንጅ፡፡ ወንጅል ከሆነ ግን ከሰዎች የበለጠ ከሱ በጣም ይርቁ ነበር፡፡ የአለህ መልክተኛ ለራሳቸው አንድም ቀን በቀል ፈጽመው አያውቁም፡፡ የአላህ ወሰኖች የሚደፈሩ ሲሆን እንጅ፡፡ ያን ጊዜ ለአላህ ወሰኖች ክብር ይበቀላሉ፡፡)

እዚህ ላይ ከነብያችን (ሰ.0.ወ.) ሕይወት ታሪክ ወደ አላህ (ኢ.ወ.)እምነት በብልሃትና በመልካም ግሳጼ ጥሪ ሲያደርጉ በነበረበት ወቅት ስለነበሩ የነብያችን ሰ.0.ወ.) አቋሞች አንዳንድ ምሳሌዎችን እንጥቀስ፡፡ (ከርሳቸው አላህ ይውደድና) አነስ ኢብን ማሊክ የሚከተለውን አውርተዋል፡ ‹ከእለታት አንድ ቀን ከነበያችን (ሰ.0.ወ.) ዘንድ በነበርኩበት ወቅት አንድ ሰውየ መጠና እንድህ አለ፡፡ እኔ ቅጣት የሚያሰከትል ወንጅል ፍጽሚያለሁና ቅጣቱን ፈጽሙበኝ አለ፡፡ ምን ዓይነት ወንጀል እንደፈጸ አልጠየቁትም፡፡ ስግደት ሣዓት ደረሰና ከነብያችን ጋር ሰገደ፡፡ ሶላቱን ከጨረሱ በኋላ ወደነብያችን (ሰ.0.ወ.) ቀረበና የአላህ ምልክተኛ ሆይ! እኔ ቅጥት የሚያስከትል ወንጀል ፈጽሚያለሁና የአላህን ትእዛዝ ይፈጽሙብኝ አለ፡፡ አሳቸውም (እኛ ጋር ሰግደሃል አይደለም እንዴ? አሉት፡፡ አሱም አዎን አለ፡፡ ያን ጊዜ አላህ ወንጀልህን ምሮልሃል አሉት፡፡›

(ከርሳቸው አላህ ይውደድና) አቡ ሁረይራ የሚከተለውን አውርተዋል፡ (አንድ ቀን አንድ ዘላን አረብ እመስጊድ ውስጥ እያለ ተነሳና ሽንቱን ሸና፡፡ ሰዎችም ሊያቋርጡት ተነሱ፡፡ ያን ጊዜ ነብያችን (ሰ.0.ወ.) (ተውት ከሽንቱ ቦታም ሽንኬሎ ወይም አኮሌ ውሃ አፍሱበት እንንተ የተላካችሁት እኮ የምታቃልሉ ስትሆን ነው፡፡ የምታከብዱ ሆናችሁ አልተላካችሁም፡፡) አሉ፡፡ እናታችን አዒሻም እንድህ ብለዋል፡ ‹የአላህ መልክተኛ አንድ ቀን አንድ ህፃን ተሰጣቸው፡፡ አቅፈውት እያለም እልብሳቸው ላይ ሽንቱን ሸና፡፡ ያለህ መልክተኛ ውሃ አምጡልኝ አሉና እሽንቱ ቦታ አፈሰሱበት፡፡›

ሙዓዊያ ኢብን አልሐከም አሰለሚ የታበሉት ባልደረባም የሚከተለውን አውርተዋል፡ ‹ከእለታት አንድ ቀን እኔ ከአላህ መልክተኛ ጋር እየሰግድሁ ሳለ ከሰዎች አንድ አስነጠሰው፡፡ አላህ ይዘንልህ አልኩኝ፡፡ ሰዎችም በግልምጫ ሲመለከቱኝ አየሁ፡፡ እኔም በምን ምክኒያት ነው እንደዚህ የምትገለምጡኝ አልኩኝ፡፡ በእጆቻቸው ጭኖቻቸውን መምታት ጀመሩ፡፡ ዝም እንድል መልክት በሰጡኝ ጊዜም ዝም አልሁኝ፡፡ እናትና አባቴ ቤዛቸው ይሁኑና የአላህ መልክተኛ ስግደት ከጨረሱ በኋላ ከሳቸው በፊትም ይሁን በኋላ ከሳቸው የበለጠ መልካም አስተማሪ አይቼ አላውቅም፡፡ በአላህ ይሁንብኝ አልገላምጡኝም፣ አልመቱኝም እንዲሁም አልሰደቡኝ፡፡ ነግር ግን እንዲህ አሉኝ፡ (ይህ ስግደት በሱ የሰዎች ንግግር ተስማሚ አይሆነውም፡፡ በሱ የሚስማማው ጌታን ማጥራት፣ ማክበርና ቁርኣን ማንበብ ነው፡፡)

የጌታችንን (ሱ.ወ.) መጽሐፍና የነብያችንን (ሰ.0.ወ.) ፈለጎች በምንከታተለበት ጊዜ በማንኛውም መልኩ ጸንፈኝነትንና ማጋነን ድባቅ የሚመቱ የተላያዩ የመቻቻል፣ ነገሮችን የማቃለልና የማግራት ገጽታዎች የምናገኝ መሆኑን አያጠራጥርም፡፡

በአሁኑ ወቅት በአለም ዙሪያ ውጥረት እየፈጠረ ያለውን ህውከት ብንምለከት የእስልምና እምነት በማንኛውም መልኩ ከመንስኤዎቹ አንዱ ነው ሊባል አይችልም፡፡ በመሰረተ እምነት በኩል

እስልምና ማንንም በእምነቱ እንዲገባ አያስገድድም፡፡ ይልቁንም ለሁሉም የእምነት ነፃነት ዋስትና ሰጥቷል፡፡ አላህ (ሱ.ወ.) እንድህ ይላል፡

{لا إِكْرَاهَ فِي الدِّينِ قَدْ تَبَيَّنَ الرُّشْدُ مِنَ الْغَيِّ}

ትርጉሙም (በሃይማኖት ማስገደድ የለም፡፡ ቅኑ መንገድ ከጠማማው በእርግጥ ተገለጠ፡፡) ማለት ነው፡፡ እንድሁም እንድህ ይላል፡

{وَلَوْ شَاءَ رَبُّكَ لَآمَنَ مَن فِي الْأَرْضِ كُلُّهُمْ جَمِيعًا أَفَأَنتَ تُكْرِهُ النَّاسَ حَتَّىٰ يَكُونُوا مُؤْمِنِينَ. }

ትርጉሙም (ጌታህም በሻ ኖሮ በምድር ያሉት ሰዎች ሁሉም የተሰበሰቡ ሆነው ባመኑ ነበር፡፡ ታድያ አንተ ሰዎችን አማኞች እንድሆኑ ታስገድዳለህን? ) ማለት ነው፡፡

በአምልኮት በኩልም ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) ከማጥበቅ ርቀን እንዲናገራና ቀለል እንዲናደርግ እንድህ በማለት ጥሪ አስተላልፈዋል፡ (ከናንተ መካከል ሰዎችን የሚያስደነብሩ አሉ፡፡ ሰዎችን በስግደት የሚመራ ሰው ቀለል ያደርግ፡፡ ከነሱ መካከል በሽተኛ፣ ደካማና አፋጣኝ ጉዳይ ያለው ሰው አለና፡፡ )

አንዳንድ ሰዎች (ከርሳቸው አላህ ይወደድና) ሙዓዝ ሶላት እያስረዘሙብን ነው ብለው አቤቱታ ባቀረቡ ጊዜ ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) በማስተማር መልኩ እንድህ አሏቸው (ሙዓዝ ሆይ! አንተ ፈተና ፈጣሪ ነህንዴ ሦስት ጊዜ ከደጋገሙ በኋላ አነዚህን ምእራፎች፡

( وَالشَّمْسِ وَضُحَاهَا)،و(سَبِّحِ اسْمَ رَبِّكَ الأَعْلَى)

እና የመሳሰሉትን አንብብ አሏቸው) በአንዳንድ ወሬዎች (ካንተ በኋላ አረጋዊ፣ ደካማና አፋጣኝ ጉዳይ ያለው ሰው ይሰግዳልና) የሚል አረፍተ ነገር ተካቶ ይገኛል፡፡ (ከርሳቸው አላህ ይውደድና) አነስ ኢብን ማሊክ እንድህ ሲሉ አውርተዋል፡ ‹አንድ ቀን ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) እመስጊድ ገቡ ከመስጊዱ ሁለት ወጋግራዎች መካከል ተወጥሮ የታሰረ ገመድ አዩ (ይህ ገመድ መንድን ነው? ) ሲሉ ጠየቁ፡፡ ይህ የዘይነብ ገመድ ነው በምትደክምበት ጊዜ የምትደገፍበት አሏቸው፡፡ ያን ጊዜ ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) (አይሆንም በሉ ፍቱት አንዳችሁ ንቃት እስካለው ድረስ ይሰገድ ከደከመው ደግሞ ይቀመጥ) አሉ፡፡

(ከርሳቸው አላህ ይውደድና) ጃቢር የተባሉት ባልደረባ እንድህ ሲሉ አውርተዋል፡ (ከእለታት አንድ ቀን መንገድ ወጣን ከኛ መካከል አንዱን ሰውየ ድንጋይ ራሱን ፈነከተው፡፡ ሌሊትም ሰውነቱን መታጠብ ግድ የሚያደርግ ሕልም አየ (በሕልሙ ፍተወት ፈሰሰው) ተየሙም ማደረግ የሚፈቀድልኝ መሆኑን የሚያቅ ሰው አለን? ሲል ባልደረቦቹን ጠየቀ፡፡ አንተ ውሃ ሳታጣ ተየሙም ማድረግ የሚፈቀድልህ ለመሆኑ የምናውቀው ነገር የለም አሉት፡፡ ሰውነቱን ታጠበ በሱም ምክኒያት ሞተ፡፡ በተመለስንም ጊዜ ለነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) ስለጉዳዩ ተነገራቸው፡፡ ያን ጊዜም (አላህ ይግደላቸውና ገደሉት፡፡ ካለወቁ አይጠይቁም ነበርን የበሽታ ፈውሱኮ መጠየቅ ነው፡፡ እሱ ማድረግ የነበረበት ቁስሉን በራፊ ማሰርና እሱን አብሶ ሌላውን አካሉን መታጠብና ተየሙም ማድረግ ነበር፡፡) አሉ፡፡

ዑምራን ኢብን ሑሶይን የተባሉት ባልደረባ በታመሙ ጊዜ ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) እንድህ የሚል መመሪያ ሰጧቸው፡ (ቁመህ ስገድ፡፡ ባትችል ደግሞ ተቀምጠህ ስገድ፡፡ አቅም ካጣህ በጎንህ ተኝተህ ስገድ፡፡) ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) አንድህ ብለዋል፡ ( ምድር ለኔ መስገጃና ንጹህ ተደርጋልኛለች፡፡ ከህዝቦቼ ማንኛውም ሰው የስግደት ወቅት በደረበት ጊዜ (በየትኛውም ቦታ) ይስገድ፡፡

ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) መቻቻልንና ገርነትን በተጨባጭ በተግባር በማሳየታቸው ለእስልምና ታላቅነት ብርሃን የሚሰጥ አንፀባራቂ ስእል ሆኖ እናገኘዋለን፡፡ ነብያችን ሶ.ዐ.ወ.) እንድህ ይላሉ፡ (እኔ ስግደት ስገባ ለማስረዘም አስብና የህፃናትን ለቅሶ እሰማለሁ፡፡ በዚህን ጊዜ በለቅሶው የእናቱን ቀልብ መንጠልጠል በማወቄ አሳጥራለሁ፡፡)

ከሰዎች መካከል ባሉት ውሎች በኩል ደግሞ የእስልምና ህግ ከሰዎች ጋር ግብይት ስናደርግና ስንፋረዳቸውም ችግርና ጭንቀትን አስወግደን መቻቻልንና ገርነትን እንድንከተል ያዛል፡፡ አላህ (ሱ.ወ.) እንደህ ይላል፡

{يَا أَيُّهَا الَّذِينَ آمَنُوا لَا تَأْكُلُوا أَمْوَالَكُمْ بَيْنَكُمْ بِالْبَاطِلِ إِلَّا أَنْ تَكُونَ تِجَارَةً عَنْ تَرَاضٍ مِنْكُمْ لَا تَقْتُلُوا أَنفُسَكُمْ إِنَّ اللَّهَ كَانَ بِكُمْ رَحِيمًا}

ትርጉሙም (እናንተ ያመናችሁ ሆይ! ገንዘቦቻችሁን ከመካከላችሁ ያለአግባብ አትብሉ፡፡ ግን ከናንተ በመዋደድ የሆነችውን ንግድ (ብሉ) ነፍሶቻችሁንም አትግደሉ፡፡ አላህ ለናንተ አዛኝ ነውና፡ ፡) ማለት ነው፡፡ እንድሁም እንድህ ላል፡

{وَإِنْ كَانَ ذُو عُسْرَةٍ فَنَظِرَةٌ إِلَى مَيْسَرَةٍ وَأَنْ تَصَدَّقُوا خَيْرٌ لَكُمْ إِنْ كُنْتُمْ تَعْلَمُونَ}

ትርጉሙም (የድህነት ባለቤት የሆነም (ባለእዳ) ሰው ቢኖር እማግኘት ድረስ ማቆየት ነው፡፡ (በመማር) መመጽወታችሁም ለናንተ በላጭ ነው፡፡ የምታውቁ ብትሆኑ፡፡ (ትሰሩታላችሁ) ማለት ነው፡፡

ነብያችን (ሰ.ዐ.ወ.) እንድህ ይላሉ፡ ( ሲሸጥ፣ ሲገዛና ሲፋረድም ገራገር የሆነን ሰው አላህ አዝነትን ይለግሰው፡፡) እንድሁም እንድህ ይላሉ፡ (በሚፋረድ ወይም በሚፋረዱት ወቅት ገራገር የሆነን ባሪያ አላህ ይዘንለት፡፡) በግብይት ገራገር መሆን ማለት በሽያጭ ሻጩ ስግብግብ፣ ለትርፍ ዋጋ ሰቃይ፣ እቃን በሞኖፖል ያዥና በሚዛን አጭበርባሪ አለመሆን ማለት ሲሆን በግዥም ገዢው ለሻጩ ገርና የሰዎችን ገንዘብ የማያጎድል መሆኑ ነው፡፡ በመፋረድ ገርነት ማለት ደግሞ አንድ ሰው ሙብቱንና ብድሩን በሚጠይቅበት ወቅት ልዝብ፣ ገርና ትእግስተኛ መሆኑ ነው፡፡

ነብያችን (ሰ.ኢ.ወ.) በመዋዋል ገርነትና ታጋሽነት በመጭው አለም ከቅጣት መዳኛ እንደሚሆን እንደህ በማለት አብስረዋል፡ (አንድ ሰው በሚፋረድና በየሚፋረዱትም ጊዜ ገር በመሆኑ ገነት ገብቷል፡፡) አሁንም እንድህ ይላሉ፡ (ከናንተ በፊት ከነበሩት ህዝቦች አንድ ሰው በጌታ ፊት ለሂሳብ ቀረበ፡፡ ምንም ዓይነት መልካም ሥራ አልተገኘለትም፡፡ ነገር ግን እሱ ከሰዎች ጋር ይቀላቀል ነበር ባለጸጋም ነበርና አገልጋዮቹ የሚከፍለው የሌለውን ሰው እዳ ከፈል ብለው ከመያዝ እንዲያልፉት ያዘ ነበር፡፡ ነብያችን አላህ (ሱ.ወ.) እንደህ አለ አሉ በዚህ አይነቱ ተግባር እኛ ከሱ ተቀዳሚዎች ነን እለፉት፡፡)

ነብያችን (ሰ.ዐ.ወ.) ከአለተ ቂያማ እይታዎች አንዱን ሲገልጹ እንድህ ብለዋል፡ ( አላህ (ሱ.ወ.) እንድህ ይላል፡ እስኪ እሳት ውስጥ ተመልከቱ አንድ ጊዜ እንኳ ቢሆንም መልካም ሥራ የሰራ ሰው ታገኛላችሁ እንዴ? አነሱም አንደ ሰው ያገኛሉ አንድ ቀን አንኳን ቢሆን መልካም ሥራ ሰርተህ አታውቅም? ሲሉ ጠየቁት፡፡ እሱም የለም ነገር ግን በሽያጭ ለሰዎች ገር ነበርሁኝ አለ፡፡ ያን ጊዜ አላህ (ሱ.ወ.) ለባሪያ ገር እንደሆነ ሁሉ ለባሪያ ገር ሁኑ አለ፡፡)

ይህን ቃሌን ተናገርሁኝ፡፡ ለኔና ለናንትም ከአላህ ዘንድ ምህረትን እለምናለሁ፡፡

* * *

ምስጋና ለአለማቱ ጌታ ለአላህ ይገባው፡፡ የአላህ እዝነትና ሰላምም በነብያትን በአላህ መላክተኞች መደምደሚያ በሰዪና ሙሐመድ በቤተሰቦቻቸውና በመላ ባልደረቦቻቸው ይውረድ፡፡

**ሙስሊም ወንድሞች ሆይ!**

በእስልምና እምነት የመቻቻልና ገርነት መርህ ሙስሊሞች ከመካላቸው በሚያደርጉት ውል ብቻ አይወሰንም፡፡ ይልቁንም ሰዎችን በሙሉ የሚያካትት አጠቃላይ የሕይወት ስርኣት ነው፡፡ አላህ (ሱ.ወ.) ምእምናን ባሮቹ ከመላ ሰዎች ጋር ያለቸው መስተጋብር መልካም እንዲሆን በማዘዝ እንድህ ይላል፡

{وَقُولُوا لِلنَّاسِ حُسْنًا}

ትርጉሙም( ለሰዎችም መልካምን ተናገሩ፡፡) ማለት ነው፡፡ እንድሁም እንድህ ይላል፡

{لاَ يَنْهَاكُمُ اللَّهُ عَنِ الَّذِينَ لَمْ يُقَاتِلُوكُمْ فِي الدِّينِ وَلَمْ يُخْرِجُوكُمْ مِنْ دِيَارِكُمْ أَنْ تَبَرُّوهُمْ وَتُقْسِطُوا إِلَيْهِمْ إِنَّ اللَّهَ يُحِبُّ الْمُقْسِطِينَ}
ትርጉሙም (ከነዚያ በሃይማኖት ካልተጋደሏችሁ ከአገሮቻችሁም ካላወጧችሁ (ከሃዲዎች) መልካም ብትውሉላቸውና ወደርነሱ ብታስተካክሉ አላህ አይከለክላችሁም፡፡ አላህ ትክክለኞችን ይወዳልና፡፡) ማለት ነው፡፡ አብደላህ ኢብን ዑመር የተባሉት ባልደረባ ፍየል ባረዱ ጊዜ ለአገልጋያቸው ለይሁዳው ጎረቤታችን ስጦታውን ልከሃልን? አረፍተነገሩን ከደገሙለት በኋላ እኔ የአላህ መልልክተኛ (ሶ.ዐ.ወ.) እንድህ ሲሉ ሰምቻለሁ፡ (ጅብሪል ስለጎረቤት አደራ ማለቱን አላቋረጠም እኔ ባንድ ወቅት መናልባትም ከንብረትህ ይውረስ ይለኝ ይሆን ብየ እስከመጠራጠር ደርሼ ነበር፡፡) አሉት፡፡
ከገርነት ገጽታዎች አንዱ የነፍስ ገርነት ነው፡፡ ማለትም ነፍስ ቸር፣ ለጋስመሆኗና ለሁሉም ሰው መልካም ውለታ መዋሏ ማለት ነው፡፡ (አላህ ይዘንላቸውና) ኢማሙ አሻፊዒ እንድህ ይሉ ነበር፡
በቸርነት ተደበቅ፡፡ ማንኛውም ነውር በቸርነት ይሰወራል እንድሉ፡፡
ለጠላቶች በምንም አይነት ውርደትን አታሳይ፡፡ የጠላቶች መሳለቅ መከራ ነውና፡፡
ከስግብግብ ገርነትን አትጠብቅ፡፡ ጥመኛ ከእሳት ውስጥ ውሃ ሊያገኝ አይችልምና፡፡
ጌታችን ሆይ! ሃይማኖታችንን በተተካከለ መልኩ መረዳትን ስጠን፡፡ ቅኑን መንገድ ምራን፡፡ በኛ ሰዎችን ቅኑን መንገድ እንድመሩም አድርግ፡፡ ቅኑን መንገድ ለተመራም ሰው የቅን መንገድ መመራቱ ምክኒያት አድርገን፡፡